## ምዕራፍ 8

# መንፈስ ቅዱስ - ክርስቲያኖችን የሚቀድሰውና የሚያበረታታው

ጆን ኒውተን በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ የከፋ ሰው ነበር። ሰዎችን በመሸጥ ገንዘብ የሚያከማች ባርያ ፈንጋይ ነበር። ይህም ሆኖ፥ አሁን ጆን ኒውተንን የምናስታውሰው በእነዚህ ተግባራቱ አይደለም። ይልቁንም፥ «ድንቅኛ ጸጋ» ("Amazing Grace") የሚለውን ጨምሮ አያሌ ውብ መዝሙሮችን የደረሰ መንፈሳዊ የቤተ ክርስቲያን መሪ በመሆኑ እናስታውሰዋለን። በጆን ኒውተንና እርሱን በሚመስሉ በርካታ ሰዎች ሕይወት ይህንን ታላቅ ለውጥ ያመጣው ማን ነው? መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ባሕርይና ጠባይ በመለወጥ ይበልጥ ክርስቶስን እንዲመስሉ የማድረግ ኃይል አለው (2 ቆሮ. 3፡18፤ ኤፌ. 3፡20)።

የሐዋርያትን ሥራ መጽሐፍ ስናነብ፥ ምንም እንኳ ዓለም ሙሉ ለሙሉ ማለት ይቻላል ህልውናውንና ተግባሩን ባያውቅም (ዮሐ. 14፡17)፥ ዛሬ በዓለም ውስጥ ከሁሉም በላቀ ሁኔታ የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ እንረዳለን። አራቱ ወንጌላት በክርስቶስ ሕይወትና ተግባራት ላይ ሲያተኩሩ፥ የሐዋርያት ሥራ ግን በቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በኩል መንፈስ ቅዱስ በሠራው ሥራ ላይ ያተኩራል። የሉቃስ ወንጌል መንፈስ ቅዱስን አሥራ ሁለት ጊዜ ሲጠቅስ፥ ይህ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ከሁሉም የላቀው ድግግሞሽ ነው። ይኸው ጸሐፊ ሉቃስ፥ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ መንፈስ ቅዱስን 42 ጊዜ ደጋግሞ ጠቅሶታል።

ከዚህ እንደምንረዳው ዛሬ በቤተ ክርስቲያንና በግለሰብ ክርስቲያኖች ሕይወት በቀደምትነት በመሥራት ላይ የሚገኘው መንፈስ ቅዱስ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖችን ሊያስደንቅ ቢችልም፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፥ መንፈስ ቅዱስ በማያምኑ ሰዎችም መካከል በከፍተኛ ደረጃ በመሥራት ላይ ይገኛል። በዮሐንስ 16፡8 ኢየሱስ፥ «እርሱም [መንፈስ ቅዱስ] መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል» ይላል። ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው፥ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው በመውቀስ ይቅርታ ወደሚያገኙበት ወደ ኢየሱስ የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜም በዓለም ሁሉ ስለሚገኝ፥ ከእርሱ

ለመሸሸግ የሚችል ማንም የለም። መዝሙር (139)፡7-10፥ «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ኮከብ ብወስድ፥ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥ ቀኝህም ትይዘኛለች» ይላል።

ኢየሱስ በዕለተ-ብዓለ-ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ላይ በወረደ ጊዜ ከሚፈጽመው ተግባር የተነሣ፥ የእርሱ ከዓለም መሄድ ለጥቅማችን እንደ ሆነ ተናግሯል። ይህም የሆነው ኢየሱስ ባይሄድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስለማይመጣና ኢየሱስ ከሄደ ግን መንፈስ ቅዱስን ለክርስቲያኖች ስለሚልክ ነው (ዮሐ. 16፡7)። ኢየሱስ ቢሄድና መንፈስ ቅዱስ ቢመጣ መልካም የሚሆነው ለምንድን ነው? በቀላሉ በትንሣኤ አካሉም ቢሆን፥ ኢየሱስ በአንድ ጊዜ በአንድ ስፍራ ብቻ ይገኝ ስለ ነበር ነው። በተወሰነ ጊዜ የህልውናውን ኃይልና በረከት ሊቀበሉ የሚችሉት ባቅራቢያው የሚገኙ ሰዎች ብቻ ነበሩ። ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በዓለም ክርስቲያኖች ባሉበት ስፍራ ሁሉ አለ። ይህም በመሆኑ፥ የጌታ ህልውና በረከት ክርስቲያኖች ባሉበት ሁሉ አለ!

መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? እርሱ አካል ነው? ወይስ አንዳንድ ሰዎች እንደሚያምኑት አንድ የሆነ ኃይል ነው? እውን መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው? አምላክ ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ይለያል? ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በዓለም ምን ይሠራል? ህልውናውንና ተግባሩን እንዴት ለይተን እናውቃለን? በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሻለን፡-

ሀ. መንፈስ ቅዱስ አካል እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

ለ. መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

ሐ. መንፈስ ቅዱስ ከወልድና ከአብ የተለየ አካል ነው?

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ሥራውን ለመግለጽ ከተጠቀሱት ተምሳሌቶች፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንማራለን?

ሠ. ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በማያምኑ ሰዎች መካከል ምን ይሠራል?

ረ. መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ምን ይሠራል?

ሰ. ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

ሸ. መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ እንዴት ይለውጣቸዋል?

ቀ. ለሁሉም ክርስቲያኖች በአጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ዕቅድ ምንድን ነው?

በ፡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት ነው?

## ሀ. መንፈስ ቅዱስ አካል እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ አካል ሳይሆን፥ እንዲያው ተጽዕኖ የሚያሳድር ስሜት ወይም የሆነ ኃይል እንደ ሆነ ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን መንፈስ ቅዱስ አካል እንደ ሆነ ያስተምረናል። መንፈስ ቅዱስን ለመግለጽ ያገለገለው የግሪክ ቃል «ኒውማ» ("Pneuma") ጾታዊ ገደብ ያልተደረገበት ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በዮሐንስ 16፡13 እንደምንመለከተው «እርሱ» በሚል ተውላጠ ስም ይጠራዋል፤ «እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል።» ስለ ሆነም፥ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን እንደ አካል ይገልጸዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተገለጸው፥ መንፈስ ቅዱስ የሰብአዊ አካል አሳብና ፈቃድ አለው። እርሱ ሰው የሚያደርገውን ያደርጋል። ጳውሎስና በርናባስን ለወንጌል አገልግሎት ሲጠራ ትእዛዛትን ሰጣቸው (የሐዋ. 13፡2)። መንፈስ ቅዱስ ነገሮችን ለሕዝቡ ይገልጻል። ለስምዖን የእግዚአብሔርን መሢሕ እስከሚያይ ድረስ እንደማይሞት ገልጾለታል (ሉቃ. 2፡25-26)። እንዲሁም ሐናንያና ሰጲራ ንብረታቸውን በሸጡ ጊዜ የተቀበሉትን የገንዘብ ልክ በውሸት በመናገር ማታለላቸውን ለጴጥሮስ ገልጾአል (የሐዋ. 5፡1-9)። መንፈስ ቅዱስ ለያንዳንዱ ክርስቲያን የትኛውን መንፈሳዊ ስጦታ እንደሚሰጥ ይወስናል (1 ጴጥ. 4፡10)።

ከአሳብና ፈቃድ በተጨማሪ፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ፍቅር (ሮሜ 15፡30)፥ ደስታ (ሮሜ 14፡17)፥ ኃዘን (ኤፌ. 4፡30) የመሳሰሉ ሰብአዊ ስሜቶች አሉት። መንፈስ ቅዱስ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ከነበራቸው የዓመፀኛነት አመለካከት የተነሣ ለአርባ ዓመታት በምድረ በዳ

ሲቅበዘበዙ፥ በእነርሱ ላይ የነበረውን ቁጣና ኃዘን ገልጾአል (ኢሳ. 63፡10)።

### ለ. መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደ ሆነ እንዴት እናውቃለን?

አንዳንድ ክርስቲያኖችን ጨምሮ ብዙ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር እንደሚያንስ ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይላል?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር እኩል ሆኖ ቀርቧል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታላቁን ተልዕኮ ሲሰጥ፥ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ... ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ብሏል (ማቴ. 28፡19)። ሦስት የተለያዩ ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ፥ ሦስት ስሞች ይኖሩአቸው ነበር። ይሁንና፥ አንድ አምላክ ብቻ ስላለ፥ አንድ ስም ብቻ አለ። የእግዚአብሔር ስም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት እኩል እንደ ሆኑ ገልጾአል። አብ እግዚአብሔር ነው፤ ወልድ እግዚአብሔር ነው፤ መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ነው።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ፥ ጴጥሮስ ለሐናንያ ከንብረቱ የተወሰነውን ስለ ሸጠበት ዋጋ እንደ ዋሸ ነግሮታል። ከዚያም ጴጥሮስ ሐናንያ መንፈስ ቅዱስን እንደ ዋሸ ገለጸለት (የሐዋ. 5፡3)። በዚህም ሐናንያ እግዚአብሔርን ዋሸ (የሐዋ. 5፡4)። በዚህ ታሪክ፥ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን እግዚአብሔር ብሎ ይጠራዋል። እንደ ኢሳይያስ 9፡6 የመሳሰሉ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችም ተመሳሳይ ነገር ያስተምራሉ። በ2ኛ ቆሮንቶስ 3፡17፥ ጳውሎስ፥ «ጌታ ግን መንፈስ ነው» ብሏል። መንፈስ ቅዱስ በኢሳይያስ 61፡1 እና በሐዋርያት ሥራ 8፡39 የጌታ መንፈስ ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ በ1ኛ ሳሙኤል 10፡10 እና ሮሜ 8፡14 የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሏል። በመሆኑም፥ መንፈስ ቅዱስ በብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን እንደ እግዚአብሔር ተለይቶ ታውቋል።

### ሐ. መንፈስ ቅዱስ ከወልድና ከአብ የተለየ አካል ነው?

አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ወይም ለኢየሱስ የተሰጠ ሌላ ስም እንደ ሆነ ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፥ እስኪ የኢየሱስን ጥምቀት ታሪክ እናስታውስ። በዚያን ወቅት፥ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ መሢሕ መሆኑን እንዴት እንደ ተረዳ

ገልጾአል። ዮሐንስ፥ «መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ» ብሏል (ዮሐ. 1፡32)። ዮሐንስ ኢየሱስን በተመለከተበት ተመሳሳይ የጊዜ ቅጽበት፥ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ መገለጽ አየ። ዮሐንስ ገለጻውን በመቀጠል፥ «እኔም (ክርስቶስ እንደ ሆነ) አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ፡- መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው . . . እርሱ ነው አለኝ» ብሏል (ቁ. 33)።

መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በኢየሱስ ላይ ማረፉ ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር አብም በተመሳሳይ ጊዜ፥ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ሲል ተናግሯል (ማቴ. 3፡16-17)። በዚህ ወቅት፥ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት በተመሳሳይ ጊዜ ተገኝተው የክስተቱ ተካፋዮች ሆነዋል። ይህም መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስና ከአብ የተለየ አካል እንደ ሆነ ያሳያል።

በታላቁ ተልዕኮ፥ ኢየሱስ ተከታዮቹ ሰዎችን በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ እንዳዘዛቸው አስታውስ። ይህም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የተለየና ዳሩ ግን በእኩልነት የሚኖር አካል እንደ ሆነ ያስረዳናል። በዮሐንስ 16፡7 ኢየሱስ፥ «እኔ ብሄድ ግን እርሱን (መንፈስ ቅዱስን) እልክላችኋለሁ» ብሏል። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ራሱን ከመንፈስ ቅዱስ ይለያል።

## መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ሥራውን ለመግለጽ ከተጠቀሱት ተምሳሌቶች፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንማራለን?

በመጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሎ ከመጠራቱ ባሻገር፥ በአያሌ ምስላዊ ማብራሪያዎች ተገልጾአል። እነዚህ ምስል መሳይ ማብራሪያዎች እያንዳንዳቸው ስለ መንፈስ ቅዱስና ተግባሩ ተጨማሪ ግንዛቤ ያስጨብጡናል።

### መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት (የሐዋ. 2፡3)

በዕለተ-በዓለ-ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ተከታዮች ላይ ሲወርድ ህልውናው ከተገለጸባቸው መንገዶች አንዱ «የእሳት ልሳን» በሚመስሉ ነገሮች ነበር (የሐዋ. 2፡3)። በብሉይ ኪዳን፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ህልውና ከአንድ በበለጡ ሁኔታዎች እንደ እሳት ተገልጾአል። እስራኤላውያን በሲና በረሃ ለአርባ ዓመታት ሲቅበዘበዙ፥ ጌታ

በመካከላቸው እንደ ነበረ የሚያመለክተው በቀን የደመና ዓምድ በሌሊት ደግሞ የእሳት ዓምድ ነበር (ዘኁ. 14፡14)። እግዚአብሔር ለሙሴ ሲናገር፥ እየነደደ በእሳት ከማይቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ነበር (ዘጸ. 3፡2)።

ናዳብና አብዩድ የተባሉ የካህኑ አሮን ሁለቱ ልጆች ከመገናኛው ድንኳን ፊት ለእግዚአብሔር እርሱ ያላዘዛቸውን እሳት ለማቅረብ ሲሞክሩ፥ የተፈጠረውን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልጽልናል፡- «እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው፥ በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ» (ዘሌ. 10፡2)። በዚህ ክፍል እሳቱ እንዲያደርጉ ባልታዘዙት ወይም ሥልጣን ባልተሰጣቸው ነገር ውስጥ ገብተው በመበደላቸው፥ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ወረደባቸው ያመለክታል (ዘሌ. 10፡1)።

ኤልያስ ግን ጸሎታቸውን ሰምቶ ለመሥዋዕትነት የቀረበውን በሬ በእሳት እንደሚበላ በመጠየቅ የበዓል ነቢያትን በተፈታተነ ጊዜ፥ እግዚአብሔር እሳት በማውረድ ኤልያስ በመሠውያው ላይ ያስቀመጠውን ሥጋ አቃጠለ፤ ይህም የሆነው የበዓል ነቢያት እስከ እኩለ ቀን ድረስ ያለ ምንም ውጤት ሲጮኹ ከዋሉ በኋላ ነበር (1 ነገሥት 18፡23-39)። በዚህ ጊዜ፥ እሳቱ የኤልያስ መሥዋዕት ተቀባይነት ማግኘቱንና በበዓል ባህላዊ ካህናት ላይ ፍርድ መገለጹን አጣምሮ የሚያሳይ ይመስላል።

እሳት የተጣበቁባቸውን ቆሻሻዎች በማስወገድ የከበሩ ማዕድናትን እንደሚያነጻ ሁሉ፥ አላስፈላጊ ነገሮችን በማስወገድ መንጻትን ያስገኛል። መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት በመገለጹ አማካኝነት የማንጻት (የመቀደስ) ሥራው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸ ይመስላል። ነቢዩ ሚልክያስ (በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተፈጸመው) የክርስቶስ አገልግሎት «እንደ አንጥረኛ እሳት» እንደሚሆን አመልክቷል (ሚል. 3፡2)። መጥምቁ ዮሐንስም ስለ ኢየሱስ ሲናገር አማኞችን «በመንፈስ ቅዱስና በእሳት» እንደሚያጠምቅ ገልጾአል (ማቴ. 3፡11)፤ ይህም ከኃጢአት መንጻትን (መቀደስን) ያመለክታል።

## መንፈስ ቅዱስ እንደ ሕያው ውኃ (ዮሐ. 7፡38)

ኢየሱስ እርካታ እርቋት ባዶነት ለተጫናት ሳምራዊት ሲናገር፥ ጥልቅ መሻቶቿን የሚሞላ ሕያው ውኃ እንደሚሰጣት ገለጸላት (ዮሐ. 4፡10-

14)። በአይሁድ የቂጣ በዓል ፍጻሜ ላይ፥ ኢየሱስ አሁንም ገና ተጠምተው ለነበሩት (ላልረኩት) የራሳቸውን ጥልቅ መሻቶች ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የሌሎችንም ጉድለቶች የሚሞላ ሕያው ውኃ እንደሚሰጣቸው ተናግሯል (ዮሐ. 7፡37-38)። በዚህ ወቅት፥ ኢየሱስ ይኸው ሕያው ውኃ በእርሱ ለሚያምኑት የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ገልጾአል (ዮሐ. 7፡39)።

በሕዝቅኤልና ራእይ መጻሕፍት፥ በሰማይ የመንፈስ ቅዱስ መኖር እንደ ሕይወት ውኃ ወንዝ፥ እንደ ብርሌ የጠራ፥ ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚፈስና በሚፈስበትም አቅጣጫ ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ሆኖ ታይቷል (ሕዝ. 47፡1-9፤ 22፡1፥ 17)። በእነዚህ ምንባቦች፥ ዝናብና ውኃ ለበረሃ ሕይወት እንደሚሰጡ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሰውን ልብ የጠለቁ መሻቶች እንደሚያረካ ሕያው ውኃ፥ ሕይወት ላልነበረባቸው ሰዎች ሕይወትንና ፍሬያማነትን ሲያመጣ ይታያል።

ምናልባትም በውኃ እንድንጠመቅ የታዘዝነው፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሕያው ውኃ ስለ ተጠቀሰ ይሆናል (ማቴ. 28፡19)፤ ይህም መንፈስ ቅዱስ እንዳጠመቀንና በክርስቶስ አካል ውስጥ እንዳስቀመጠን ለማመልከት ነው (1 ቆሮ. 12፡13)። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት «ከአንዱ መንፈስ (ሕያው ውኃ)» እንዳጠጣን ተጠቅሶአል።

### መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ (ዮሐ. 1፡32)

ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወረደ (ሉቃ. 3፡22)። ርግብ ንቁ፥ የዋህና ጎጂ ባሕርይ የሌላት ወፍ ነች። በዕብራውያን መጽሐፍ፥ ኢየሱስ «ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት» እንደ ሆነ ተገልጾአል (ዕብ. 7፡26)። ከሰዎች ሁሉ በላይ ኢየሱስ በከፍተኛ ደረጃ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶአል። በጥምቀቱ ጊዜ የርግብ መውረድ፥ ማንም ሰብአዊ ሰው ለመቼውም ሊያደርግ በማይችል ሁኔታ የሰውን ልጆች የልብ ጉድለቶች የሚረዳውንና የሚጠነቀቅላቸውን የዋህ፥ ጎጂ ባሕርይ የሌለውና ሩኅሩኅ የእግዚአብሔር መንፈስ ልብ በክርስቶስ ውስጥ ያሳያል።

በተጨማሪም፥ ርግብ በሙሴ ሕግ መሠረት ድሀ ሰው ለኃጢአት መሥዋዕት የሚያቀርባት ትንሿ መሥዋዕት ነበረች (ዘሌ. 5፡7)። ይህም

ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በምድር ላይ የመጨረሻው ድሀ ሳይቀር ሊጠቀምበት የሚችል የኃጢአት መሥዋዕት መሆኑን ያሳያል (ዕብ. 9፡14)።

## መንፈስ ቅዱስ እንደ ተቀደሰ ዘይት (ሉቃ. 4፡18)

በብሉይ ኪዳን፥ እግዚአብሔር የመገናኛውን ድንኳን ዕቃዎችና ካህናቱ ራሳቸውን ለመቀባት ቅዱስ ዘይት እንዲያዘጋጁ አዘአል (ዘጸ. 30፡22-30)። ይህ ዘይት ለሌላ ለማንኛውም ዓይነት ዓላማ ሊውል አይችልም ነበር (ዘጸ. 30፡32-33)። ኢየሱስ፥ «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል» ብሏል (ሉቃ. 4፡18-19)። ጥቅሱ እንደሚል፥ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ስለ ተቀባ፥ እነዚህን አገልግሎቶች አከናውኗል። የብሉይ ኪዳን የሥርዓት ሕግ ተምሳሌታዊ ደንቦች ሲጠኑና ከግንዛቤ ሲውሉ፥ የቅባት ዘይቱ የመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት አይሳትም።

በብሉይ ኪዳን ነገሥታትም በተቀደሰው ዘይት ይቀቡ ነበር። ንጉሥ ዳዊትን በተመለከተ፥ ሳሙኤል ወጣቱን ዳዊትን በአባቱና ወንድሞቹ ፊት በተቀደሰው ዘይት ከቀባበት ዕለት አንሥቶ፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኃይል» እንደ መጣ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል (1 ሳሙ. 16፡13)።

ሰባት ቅርንጫፎች የነበሩት የመገናኛው ድንኳን መብራት ከንጹሕ የወይራ ዘይት የማያቋርጥ ብርሃን ይሰጥ ነበር (ዘጸ. 27፡20)። መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ በምሥጢር የሚኖርና ክርስቲያኑ በኃጢአት ለጨለመች ዓለም ግብረ-ገባዊና መንፈሳዊ ብርሃን እንዲፈነጥቅ የሚያስችለው ነው (ማቴ. 5፡14-16)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ ዘይት መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል። ይህም በአማኙ ልብ ያደረው መንፈስ ቅዱስ፥ በክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ የመንፈሳዊ ኃይልና ብርሃን ድብቅ ምንጭ እንደ ሆነ ያስረዳናል። በመንፈስ ቅዱስ ሀልውና አማካኝነት፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነበር (ዮሐ. 8፡12)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን

ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና» ይላል (የሐዋ. 10፡38)።

### መንፈስ ቅዱስ እንደ ነፋስ (ዮሐ. 3፡8)

የግሪክ ቃል «ኒውማ» በጥቅሉ ዓውደ ንባብ ላይ በመመሥረት፥ «ነፋስ» ወይም «መንፈስ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ ጋር ሲነጋገር፥ ይህንኑ የትርጉም መመሳሰል ገልጾአል። «ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው» (ዮሐ. 3፡8)።

ነፋስ በእርጋታ እየነፈሰ ሕይወትን እንደሚያድስ ሁሉ፥ ከፍተኛና ለመቋቋም የሚያዳግትም ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በነፋስ ተምሳሌትነት መገለጹ ከፍተኛ ትርጉም አለው። ነፋስ የማይታይ ሆኖ፥ ዳሩ ግን ውጤቱ በቀላሉ ከዓይን ሊገባ እንደሚችል ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም የክርስቶስን ወንጌል በዓለም ሁሉ ያሰራጫ ታላቅና የማይታይ የእግዚአብሔር ነፋስ ነው። በዕለተ-በዓለ-ሃምሳ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ከተገለጸባቸው ሁኔታዎች አንዱ «ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ» መምጣቱ ነው (የሐዋ. 2፡2)። እንዲሁም፥ መንፈስ ቅዱስ በጌታ ለመነቃቃት ለሚሹ ክርስቲያኖች፥ የማይታይ አነቃቂ መንፈሳዊ እስትንፋስ ነው።

## ሠ. ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በማያምኑ ሰዎች መካከል ምን ይሠራል?

### መንፈስ ቅዱስ በዓለም የክፋትን መበራከት ይከለክላል

ዛሬ በዓለም ውስጥ መንፈስ ቅዱስና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ባይኖሩ ኖሮ፥ በዚህች ዓለም ለመኖር አይቻልም ነበር። የሰዎች ልብ በትክክል ምን እንደሚመስል ሙሉ ለሙሉ ስለማንረዳ፥ ዕድሉ ቢያጋጥማቸው ምን እንደሚያደርጉ አናውቅም።

መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ለማድረግ ከሚፈልጓቸው ክፋቶች ብዙዎቹን ይከለክላል። ምናልባት በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡7 ሥርዓት-አልበኝነትን እንደሚከለክል ሆኖ የተገለጸው ይኸው መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን አይቀርም። በዘፍጥረት፥ አቤሜሌክ ሣራን ለሚስትነት በወሰደ ጊዜ፥ እግዚአብሔር

አቢሜሌክን ከአብርሃም ሚስት ጋር እንዳያመነዝር እንደ ከለከለው ይናገራል (ዘፍጥ. 20፥6)።

ዛሬ በዓለም ውስጥ ብዙ ወንጀልና ጭካኔ ተበራክቶ ስለሚታይ፥ መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ክፋት እንደማይከለክል ግልጽ ነው። ይሁንና፥ መንፈስ ቅዱስ ክፋትን የመቋቋም ተግባሩን ከመቅጽበት ቢያቆም ኖሮ፥ ዓለም ለመኖር የማይቻልባት ስፍራ ትሆን ነበር።

መንፈስ ቅዱስ ክፋትን ለመከልከል የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማል። አንዳንድ ጊዜ መንግሥትን፥ ሕግጋትንና ፖሊሶችን ይጠቀማል (ሮሜ 13፥3-4)። እንዲሁም፥ ለክርስቲያኖች ጸሎት ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ በእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ይጠቀማል (የሐዋ. 12፥3-8)። የቅዱሳን መላእክትን ሥራ በተመለከተ በምዕራፍ 10 ውስጥ የበለጠ ማብራርያ እናቀርባለን። ምናልባት መንፈስ ቅዱስ ባጠቃላይ በዓለም ክፋትን የሚከለክልበት ዋንኛው መንገድ ለሰዎች ልብ ስለ ትክክለኛና የተሳሳቱ ነገሮች በመናገርና ለተሳሳቱ ተግባራቸውም በመውቀስ ነው። ኢየሱስ፥ «እርሱም (መንፈስ ቅዱስ) መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል» ብሎአል (ዮሐ. 16፥8)። ይህም መንፈስ ቅዱስ በሰው ልጆች የትክክለኛና የተሳሳተ ግንዛቤ ውስጥ የሚሠራውን ተግባር ያመለክታል – የሕሊና ዳኝነት። ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ ነው ሰዎች ይቅርታ የሚያስፈልጋቸው ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ የሚገነዘቡት።

**መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው በመውቀስ፥ ትኩረታቸውን ወደ ክርስቶስ ይመራል**

ከመንፈስ ቅዱስ ክፋትን የመከልከል ተግባር ጋር በቅርብ ተሳስሮ የምናገኘው ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የማምጣት ሥራውን ነው። መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ለኃጢአታቸው ምላሽ የሚሰጡበት ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ያስገነዝባቸዋል። መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለኃጢአታቸው የበደለኛነት ስሜት እንዲያድርባቸው በማድረግ ሲወቅስ፥ ፍርድና የኃጢአት ቅጣትም እንደሚጠብቃቸው ያስጠነቅቃቸዋል። በዚህ እውነት ላይ በመንተራስ፥ ሰዎች ንስሐ ገብተው ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ ይለምናቸዋል (ዮሐ. 16፥8-13)።

መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአት በደለኛነታቸው በመውቀስና ክርስቶስ እንደሚያስፈልጋቸው በመግለጽ ሥራውን በታማኝነት በሰዎች ልብ ውስጥ

ባይፈጽም ኖሮ፥ ማናቸውም ንስሐ ሊገቡና በክርስቶስ ሊያምኑ አይችሉም ነበር፤ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጭ በክርስቶስ ማመን የማይቻል ነው (ዮሐ. 6:44፤ ሮሜ 8:9)።

ሰዎች ስለ ክርስቶስ ለማሰብ መፍቀዳቸውና ያደረገላቸውን ማስተዋላቸው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ኢየሱስ፥ «እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና» ብሏል (ዮሐ. 16:14)። አንድን ሰው ማክበር ማለት ወደዚያ ሰው ድንቅኛ ብቃቶች ቀልብን መሳብ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን አትኩሮት ወደ ክርስቶስና ክርስቶስ ወዳደረገላቸው ተግባር ይስባል እንጂ፥ ወደ ራሱ አይስብም (ዮሐ. 15:26)።

የሚያሳዝነው፥ ሰዎች ይህንኑ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሊቃወሙና በእግዚአብሔር ላይ ልባቸውን ሊያደነድኑ መቻላቸው ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ልባቸውን እንዳያደነድኑ ያስጠነቅቃቸዋል (ዕብ. 3:15)። ልባቸውን ካደነደኑ እነርሱን ወደ ንስሐ ማምጣት ስለማይቻል (ዕብ. 6:6)፥ ከደኅንነት ርቀው ይጠፋሉ። የሚያሳዝን እውነት ቢሆንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ልባቸውን በጣም በማደንደናቸው ሕሊናቸው ስለ ደነዘዘና የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ለመስማት ስላልቻሉት ሰዎች ይናገራል (1 ጢሞ. 4:2)። ፈርዖን በእግዚአብሔር ላይ ልቡን አደንድኖ ነበር (ዘጸ. 5:2፤ 8:15)። በአዲስ ኪዳን ፈሪሳውያንና የአይሁድ መሪዎችም ተመሳሳይ ነገር አድርገዋል (የሐዋ. 7:1-58)።

ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ልባቸውን ሲያደነድኑ የትክክለኛነትንና የስሕተተኛነትን እውነተኛ ግንዛቤ ያጣሉ። ለዚህ ነው ዛሬ ሰዎች ክፉ ተግባራቸው ግድ ሳይሰጣቸው፥ እንዲህ ዓይነት ክፉ የወንጀልና የጭካኔ ተግባራትን የሚፈጽሙት። ሰዎች ልባቸውን ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ እያደነደኑ ስለ ሆነ፥ ዓለማችን ባለማቋረጥ ጨካኝና ክፉ እየሆነች ነው።

ሰዎች ልባቸውን እንደዚህ ሲያጠነክሩ፥ ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ አድርገው ለማሰብ ይታለላሉ (1 ጢሞ. 4:2-3)። ይህ በቅርቡ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ለመጣው ወሲባዊ ግድፈትና ውርጃ አንዱ ምክንያት ነው። ሰዎች ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ድምፅ ልባቸውን እያጠነከሩ ስለ መጡ፥ እነዚህ አስከፊ ኃጢአቶች ስሕተት እንደ ሆኑ አያስቡም። በብዙ አጋጣሚዎች ስለ ክርስቶስ ቢሰሙም አልተቀበሉትም። አንድ ሰው ክርስቶስን ሲተው፥ የደኅንነትን ተስፋ ያጣና በማያቋርጥ

ምግባረ-ብልሹነት ውስጥ ይዘፈቃል። ወንጀሉ የተረጋገጠባቸው በደለኞች ለጥፋታቸው ምንም የጸጸት ምልክት ሳያሳዩ የመጨረሻ ቃላቸውን ሲሰጡ መስማት እየተለመደ መጥቷል።

## ረ. መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ምን ይሠራል?

ከፍ ብለን ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ማንም ሰው ለኃጢአቱ ንስሐ ገብቶ በክርስቶስ እንደማያምን ተመልክተናል። መንፈስ ቅዱስ ሰውን ስለ ኃጢአቱ በመውቀስ፥ ለኃጢአቱ ፍርድ እንደሚመጣበት እንዲያምን ይገፋፋዋል (ዮሐ. 16:8-11)። እንዲሁም፥ መንፈስ ቅዱስ ሰው ለኃጢአቱ ይቅርታ የሚያገኝበት ብቸኛው መንገድ ክርስቶስ እንደ ሆነ እንዲያምን ይገፋፋዋል። ስለ ሆነም፥ አንድን ሰው ወደ ለውጥ ደረጃ የሚያደርሰው መንፈስ ቅዱስ ነው።

ትክክለኛውን የመለወጥ ተግባር የሚፈጽመውም መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስ ለተማረው የአይሁድ የሃይማኖት መሪ ኒቆዲሞስ፥ «እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም (ከመንፈስ ቅዱስ) የተወለደ መንፈስ ነው» ብሏል (ዮሐ. 3:5-6)። ዳግመኛ ያልተወለደ ሰው መንፈስ በኃጢአት ምክንያት ሙት ሲሆን፥ ለዚህ ለሞተው የሰው መንፈስ ልደትና ሕይወት ለመስጠት ኃይል ያለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (ኤፌ. 2:1-2)። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለሞተ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት የመስጠቱ ተግባር «የዳግም ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ» ይባላል (ቲቶ. 3:5)። ይህ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች በግል ከሚፈጽማቸው አያሌ ነገሮች የመጀመሪያው ነው።

አንዳንድ ሰዎች ዳግም ልደት የእግዚአብሔር ሥራ ግብ እንደ ሆነ በማሰብ ይሳሳታሉ። እውነቱ ግን ዳግም ልደት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ላለው ዕቅድ የመጀመሪያው እንደ ሆነ ነው። ዳግም ልደት ልክ ወደ አንድ አዲስ አገር ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማቢያ እንደ መድረስ ነው። በአውሮፕላን ማቢያው የምንወርደው እዚያ ለመኖር አይደለም። የአውሮፕላን ማቢያው በአዲሲቱ አገር ለምናከናውናቸው አዳዲስ ተግባራት ሁሉ የመነሻ ነጥብ ብቻ ነው።

በክርስቶስ ዳግም መወለዱም ይኸው ነው። ዳግም ልደት በአዲሱ የእግዚአብሔር መንግሥት አዲስ ክስተት ነው። ከዚህ ቀደም በሰይጣን

አገዛዝ ሥር በዚህ ዓለም ውስጥ ኑረናል (ኤፌ. 2፡2)። አሁን ደግሞ በክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል (ዮሐ. 1፡12)። በኢየሱስ ክርስቶስ አገዛዝ ወደሚመራው የእግዚአብሔር መንግሥት ተሻግረናል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ከጨለማ ሥልጣን አዳነን . . . ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን» ይላል (ቆላ. 1፡13)።

መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች የሚያደርጋቸውን አያሌ ነገሮች ለመረዳት፥ እግዚአብሔር ለያንዳንዱ አማኝ የወጠነውን ዕቅድ መገንዘብ አለብን። በተጨማሪም፥ ለአማኞች ሁሉ በአጠቃላይ (ለቤተ ክርስቲያን) ያዘጋጀውን ዕቅድ መረዳት አለብን። መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ከዚያ ዕቅድ ጋር የሚዛመዱ ናቸው።

ሰ. ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ለያንዳንዱ ክርስቲያን ያለው ዓላማ እርሱ ወይም እርስዋ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመምሰል በባሕርይ እንዲለወጡ ነው (ሮሜ 8፡29)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «እኛም ሁላችን ... የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» ይላል (2 ቆሮ. 3፡18)።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ለዚህ ዓይነቱ ለውጥ ምሳሌ ይሆነናል። በገሊላ ባሕር ዳርቻ የሚኖር ያልታወቀ ዓሣ አጥማጅ ነበር። ስሜታዊ፥ ችኩል (ማቴ. 16፡22፤ ዮሐ. 21፡7) እና ተናዳጅ ሰው ነበር (ዮሐ. 20፡10)። ለኢየሱስ ስላለው ታማኝነትና ቢያስፈልግም ለእርሱ ለመሞት ዝግጁ መሆኑን በትምክህት ቢናገርም (ዮሐ. 13፡37)፥ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በባርነት በምትኖር ልጃገረድ ፊት ክርስቶስን እንደማያውቅ ክዷል (ዮሐ. 18፡17)።

ይሁንና፥ መንፈስ ቅዱስ በጴጥሮስ ሕይወት ትልቅ ተግባር ፈጽሞአል። ክርስቶስን ለገደሉት ለእነዚያው ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን የመጀመሪያ የወንጌል መልእክት ለማስተላለፍ ቻለ። በዚህም ስብከቱ፥ ሦስት ሺህ ሰዎች ዳግም ተወለዱ (የሐዋ. 2፡14-41)! በኋላም እንዲህ ታላቅ መሪ ሆኖ በመለወጡ፥ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ሊቀ-ጳጳስ እንደ ሆነ አውጃለች። በዓለም ከሚገኙ ገናና የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች አንዱ በእርሱ ስም የተጠራው የሮሙ ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ነው።

ይህም ብቻ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ፥ የጴጥሮስ ስም በሰማይ የምትገኝ ዘላለማዊት የእግዚአብሔር ከተማ የመሠረት ድንጋዮች አንዱ አካል እንደ ሆነ ይናገራል (ራእይ 21:14)። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በጴጥሮስ ሕይወት እንዲህ የላቀ በመሆኑ፥ ይህንኑ ያልታወቀ ተራ ዓሣ አጥማጅ ለዘላለም የሚከበር ታላቅ ክርስቲያን መሪ አድርጎ ለውጦታል። በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ስለ ተጠቀሰው ባርያ ፈንጋይ ጆን ኒውተንም ይህንኑ ልንል እንችላለን።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአፍሪካ ሕዝቦችም፥ ለዚሁ ሕይወት ለዋጭ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምስክርነታቸውን ሊሰጡ ይችላሉ። ከጠንቋይ፥ ከአጋንንት እስራት፥ ጭካኔ ከተሞላበት የወንጀል ተግባር፥ ከወሲብ ኃጢአት፥ ከዕፅ ሱሰኛነትና ከሌሎችም በሺህ ከሚቆጠሩ ኃጢአቶች ታድጎአቸዋል። በክርስቶስ ሙሉ አዲስ ሕይወት ሰጥቶአቸዋል። እያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን ሕይወትን ለሚለውጠው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምሳሌ ነው። የተጎሳቆለውን ኃጢአተኛ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ወደ ክርስቶስ ባሕርይ መለወጥ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው።

## ሸ. መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ እንዴት ይለውጣቸዋል?

መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ አምሳል የሚለውጠን እንዴት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን የሚያደርገው መኖሪያውን በያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ በማድረግ (በእነርሱ ውስጥ በማደር ዮሐ. 14:16-17) እንደሆነ ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ለማደር ሲመጣ፥ የኃጢአት ምኞቶቻችንን ይቃወማል፤ በመሆኑም፥ ክርስቲያኖች በውስጣቸው ከፍተኛ ግጭት ሲካሄድ ይሰማቸዋል። ገላትያ 5:17፥ «ሥጋ በመንፈስ (ቅዱስ) ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና» ይላል። ምንም እንኳ ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን እነዚህን ለውጦች በከፍተኛ ደረጃ ቢቃወምም፥ ለመለወጥና ክርስቶስን ለመምሰል መሻትና ጥንካሬን የሚሰጠን በውስጣችን ያደረው መንፈስ ቅዱስ ነው (ፊልጵ. 2:13፤ ገላ. 5:17)።

ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር የምርጫ ነፃነታችንን አይጫነውም። ልንለወጥ ከፈለግን የመንፈስ ቅዱስን ትእዛዝ ለመጠበቅ መምረጥ አለብን። ይህም ብዙ ክርስቲያኖች በባሕርያቸው ብዙ ለውጥ ለምን እንደማያሳዩ ይገልጻል፤ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ሰምቶ እንደ መታዘዝ ይቃወማሉ። ስለ ሆነም መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በመንፈስ ተመላለሱ፤ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ» በማለት ያደፋፍረናል (ገላ. 5:16)።

ራሳችን የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ለመታዘዝ ስንመርጥ ብቻ ነው እግዚአብሔር የምንለወጥበትን ብርታት የሚሰጠን። ፊልጵስዩስ 2፡13፥ «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» ይላል።

ሁኔታው የኤሌክትሪክን ብርሃን ከማብራት ጋር ሊመሳሰል ይችላል። ማብሪያውን መጫኑ ጠባያችንን ለመለወጥ ውሳኔ ከማድረግ ጋር ሊወዳደር ይችላል። በሽቦዎቹ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ካለ፥ አምፑሉ ይበራል፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ከሌለ ግን አምፑሉ አይበራም። የማያምኑ ሰዎች (በማብሪያሪያው እንደ ተጠቀሰው ማብሪያውን በመጫን) መንገዳቸውን ለመለወጥ ሊፈልጉ ይችላሉ። ይሁንና፥ (በሽቦዎቹ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ሳይኖር እንደሚችል ሁሉ) ባሕርያቸውን የሚለውጥ ኃይል ከሌለ፥ ለጥቂት ጊዜ ሊለወጡና ወዲያው ደግሞ የኃጢአት ምኞቶች ሕይወታቸውን ሊቆጣጠሩ ይችላሉ።

ባንጻሩ፥ ክርስቲያኖች ጠባያቸውን ለመለወጥ ሲፈልጉ፥ በትክክል የለውጡን ሂደት ለማገዝ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሕይወታቸው ውስጥ ይገኛል። እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሲወስኑ፥ መንፈስ ቅዱስ ጠባያቸውን እንዲለውጡ ይረዳቸዋል። ከዚያም ለሌሎችም ብርሃን ይሆናሉ። ኢየሱስ፥ «መልካሙን ሥራችሁን አይተው፥ በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» ብሏል (ማቴ. 5፡16)።

ከዓለም የተቀደስነው ወይም የተለየነው የኢየሱስ ክርስቶስን የከበረ ባሕርይ እንድናንጸባርቅ ነው። ጳውሎስ፥ «እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና፤ ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ» ሲል ጽፎአል (2 ተሰ. 2፡13-14)። እንደ እኛ ዓይነት ምስኪን ኃጢአተኞችን የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲሆኑ የመለየቱ ሥራ በዓለም የክርስትና እምነት እውነት እንደ ሆነ የሚያሳይ ታላቅ ማረጋገጫ ነው። የትኛውም ሌላ ሃይማኖት ወይም ፍልስፍና እንዲህ ዓይነቱን የማያቋርጥ የባሕርይ ለውጥ አላስከተለም - ኃጢአተኞች ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ ሊለውጥ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነውና።

ይህንኑ ኃጢአተኛ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ አምሳል የመለወጥ ታላቅ ተግባር ለመፈጸም፥ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኑና በክርስቲያኑ ውስጥ

አያሌ ነገሮችን ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ውስጥ ከሚያደርጋቸው ነገሮች ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

አዲስ ልደት - ይህ ተግባር በምዕራፍ ሰባት ተገልጾአል። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ለሚያምኑ ሰዎች መንፈሳዊ ልደትና አዲስ ሕይወት ያጎናጽፋል። ይህም ተግባር በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአያሌ የቃላት ምስሎች ተብራርቶአል። በቲቶ 3:5፥ የአዲስ ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ተብሏል። በዮሐንስ 3:3 «ዳግም መወለድ» ተብሏል። በአንደኛ ቆሮንቶስ 12:13፥ የክርስቶስ የአካል ክፍሎች በምንሆንበት በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና ከመንፈስ ቅዱስ መጠጣት ተብሏል። እነዚህ ሁሉ መግለጫዎች በዳግም ልደት ጊዜ ወደሚፈጸመው አንድ ታላቅ ተአምር ያመለክታሉ፤ በዚህም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሟቹ ሰብአዊ ነፍሳችን ለእግዚአብሔር ሕያው ይሆናል።

ማተም - በክርስቲያን ልብ ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ በዚያ ክርስቲያን ላይ የባለቤትነትን ማኅተም ያኖራል፤ በመሆኑም፥ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ አባል መሆናችን ለዘላለም ዋስትና ያለው ነው (2 ቆሮ. 1:21-22፤ ኤፌ. 1:13-14)። ይህ የባለቤትነት ማኅተም የክርስቶስ መሆናችንን ያረጋግጣል። በጥበቃው ተማምነን እንኖራለን። በተጨማሪም፥ አንድ ቀን የእግዚአብሔርን የማዳን ፍጻሜ እንደምንመለከትና ክርስቶስ ሲመለስ የትንሣኤ አካል እንደምንለብስ ዋስትና ይሰጠናል (ኤፌ. 4:30)። በዚህ ሁኔታ፥ በክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም አንድ ሰው ቢስክሌት ወይም ሌላ ዓይነት ዕቃ በሚገዛበት ጊዜ የሚከፍለው ቀብድ ዓይነት ነው። ቀብዱ የከፈለው ሰው በኋላ ሙሉውን ሒሳብ እንደሚከፍል ዋስትና ይሰጣል። የመንፈስ ቅዱስ መኖር፥ አንድ ቀን በእኛ ውስጥ የማዳን ሥራውን እንደሚፈጽም በዋስትና የሚሰጠን ቀብድ ነው (2 ቆሮ. 1:22)።

ጽናትና ብርታት – መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኑ ጽናትና ብርታት ይሰጣል (ዮሐ. 14:16፤ ኤፌ. 3:16)። ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን «አጽናኝ» ይለዋል (ዮሐ. 14:16፥ 26፤ 15:26፤ 16:7)፤ ይህም በግሪክ ጳራቅሊጦስ ሲሆን፥ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች «ረዳት» (NASB)፥ «አማካሪ» (NIV) ይሉታል። «ጳራቅሊጦስ» የሚለው የግሪክ ቃል አንድን ሰው ለመርዳት፥ ለማበረታታት፥ ለማጽናት ወይም ለመምከር ከአጠገቡ መገኘት የሚል ትርጉም አለው። ሐዋርያው ጳውሎስ አስቸጋሪ የአገልግሎት ተግባሩን

እንዲወጣ ያስቻለው ይኸው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ እንደ ሆነ ይናገራል (ቆላ. 1:29፤ 1 ቆሮ. 15:10)። በብሉይ ኪዳን፥ መንፈስ ቅዱስ ለሶምሶንና ዳዊት እንዲህ የላቀ ሥጋዊ ጽናትና ብርታት ስለ ሰጣቸው በባዶ እጃቸው አንበሳን እንደ ነተበ ጨርቅ በጣጥሰው ገድለዋል (መሳ. 14:5-6፤ 1 ሳሙ. 17:36-37)። በአዲስ ኪዳን፥ መንፈስ ቅዱስ በቀደምትነት ለክርስቲያኑ መንፈሳዊ ግብረ-ገባዊ ጥንካሬ ይሰጠዋል (ኤፌ. 3:16፥ 20)። ይሁንና፥ ለወንጌሉ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥጋዊ ጽናትና ትዕግሥትን ይሰጠዋል (ቆላ. 1:29)።

ጸሎት – ብዙውን ጊዜ ምን እንደምንጸልይ ስለማናውቅ፥ መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኑ እንዲጸልይ ይረዳዋል። መንፈስ ቅዱስ ራሱ በትክክል ለክርስቲያኑ ይጸልያል ወይም ጸሎቱን ለእግዚአብሔር አብ ይተረጉማል (ሮሜ 8:26)። ይህንንም በማድረግ፥ መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኑ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ እንዲጸልይ ያስችለዋል (ሮሜ 8:27)። አንዳንድ ጊዜም መንፈስ ቅዱስ በትክክል የክርስቲያኑን ከንፈሮች ለልሳን ስጦታ መገለጫነት በመጠቀም ይጸልያል (1 ቆሮ. 14:14-15)።

አብርሆተ– ቅዱሳት መጻሕፍት- መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላት ከማስታወሱም በላይ (ዮሐ. 14:26)፥ ለክርስቲያኑ የእግዚአብሔርን እውነት ምንነት ያበራለታል (ዮሐ. 16:13፤ 1 ቆሮ. 2:10-12)።

ምስክርነትና አገልግሎት– መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች ጌታን እንዲያገለግሉ ያነቃቃቸዋል (ፊልጵ. 2:13)። በተጨማሪም፥ ክርስቲያኑ ለክርስቶስ በሚሰጠው ምስክርነትና አገልግሎት ላይ ኃይሉን ይጨምራል (የሐዋ. 1:8፤ ቆላ. 1:29)። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለራሱ አገልግሎት ይኸው ኃይልና ድፍረት እንደሚያስፈልገው በመገንዘብ፥ ክርስቲያን ወገኖቹ እግዚአብሔር የአገልግሎት በሮችን እንዲከፍትለትና ይህንኑ ኃይል እንዲሰጠው ይጸልዩለት ዘንድ ጠይቋል (ቆላ. 4:3፤ ኤፌ. 6:19-20)። ለዚህም ነው ክርስቲያኖች ለሚሲዮናውያንና ለወንጌላውያን ዘወትር መጸለይ የሚኖርባቸው።

የመንፈስ ፍሬ – የኢየሱስ ክርስቶስን ውብ ባሕርይ ብቃቶች በክርስቲያኑ ውስጥ የሚያፈራው መንፈስ ቅዱስ ነው። እነዚህም የባሕርይ ብቃቶች «የመንፈስ ፍሬ» ይባላሉ (ገላ. 5:22-23)። በእነዚህም ውስጥ፥ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ገርነት፥ በጎነት፥ ታማኝነት፥ የዋህነትና ራስን

መንፈስ ቅዱስ - ክርስቲያኖችን የሚቀድሰውና የሚያበረታታው 
መግዛት ተካተዋል። እነዚህ ብቃቶች በሕዝቡ ውስጥ እያደጉና እየበሰሉ ሲሄዱ እግዚአብሔር በጣም ደስ ይሰኛል።

ምሪት - መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኑን በዕለታዊ ሕይወቱና ለጌታው ባለው አገልግሎት ይመራዋል (ሮሜ 8:14)። ለዚህ ተግባራዊ ምሳሌ የሚሆነን በጳውሎስ ሁለተኛ የሚሲዮናዊነት ጉዞ፥ ጳውሎስና ሲላስ በቢታኒያ ለመስበክ ሲፈልጉ ወደዚያ እንዳይሄዱ በመንፈስ ቅዱስ መከልከላቸው ነው (የሐዋ. 16:6-7)።

ምልክቶችና ተአምራት - በተለይም የክርስትና ተቃዋሚዎች በሚኖሩበት ጊዜ፥ አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ምልክቶችንና ተአምራትን በመሥራት የወንጌሉን እውነታ ያጠናክራል። ዕብራውያን 2:3-4፥ «ይህ (ደኅንነት) በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፥ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት፥ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ በምልክትና በድንቅ በልዩ ልዩ ተአምራትም፥ መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ መሰከረለት» ይላል። እግዚአብሔር ተአምራትን የሚሠራው ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስከበርና ሰዎች በክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለመሳብ እንጂ፥ ለተመልካች የዓይን እርካታ ለመስጠት አይደለም። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ጳውሎስ በጠንቋዩ ኤልማስ ላይ ያወረደው የዓይነ-ስውርነት ተአምር ነው (የሐዋ. 13:8-12)፤ ይህም የሆነው ኤልማስ ጳውሎስና በርናባስ ለቆጵሮሱ የሮም ገዥ የሚያቀርቡትን የወንጌል ስብከት በጥብቅ በመቃወሙ ነው። ይህ ተአምር የሮማው ገዥ ሰርግዩስን በክርስቶስ እንዲያምን አድርጓል (የሐዋ. 13:12)።

ውስጣዊ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት - መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ሆኑና የክርስቶስም ንብረቶች እንደ ሆኑ በልባቸው ይመሰክርላቸዋል (ሮሜ 8:16፤ 1 ዮሐ. 5:10)።

ቅባት - መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በሚገባ ያንጹ ዘንድ ቃሉን የሚያስተምሩትንና የሚሰብኩትን ሰዎች ይቀባል (1 ቆሮ. 12:28፤ 1 ቆሮ. 14:4፤ 1 ዮሐ. 2:27)።

ለአገልግሎት መጥራት - በሐዋርያት ሥራ 13:2 ጳውሎስንና በርናባስን እንደለየ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለአገልግሎት ይለያል። ይህንንም ጥሪ ለማጽናት ብዙውን ጊዜ የተጠራው ሰው ከሚገኝበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ምስክርነትና ማበረታቻ እንዲሰጡት ያደርጋል።

መንፈሳዊ ስጦታዎች - መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን አንድ ወይም ከዚያ በላይ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል (1 ጴጥ. 4፡10-11)። መንፈሳዊ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያንን በአንድ መንገድ የሚረዱ እግዚአብሔር የሰጣቸው መንፈሳዊ ችሎታዎች ናቸው። የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን መገንባት (ማጠናከርና ማነፅ) ነው (ሮሜ 12፡4-6፤ 1 ቆሮ. 12፡4-11)። በምዕራፍ ዘጠኝ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች በይበልጥ እንነጋገራለን።

ፈተናን ማሸነፍ - መንፈስ ቅዱስ ለጸሎት ምላሽ በመሆን፥ ክርስቲያኖች ፈተናዎችንና የሰይጣንን ቀጥተኛ ጥቃቶች እንዲቋቋሙ ይረዳቸዋል (ማቴ. 26፡40-41)። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና» ሲል ጽፎአል (1 ዮሐ. 4፡4)። እንዲሁም፥ ዮሐንስና ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ከሰይጣን እንደሚጠብቀን ይናገራሉ (1 ዮሐ. 5፡18፤ 2 ተሰ. 3፡3)። በምዕራፍ 12 ክርስቲያን ከጨለማው ኃይላት ጋር ስላለው ግጭት በይበልጥ እናብራራለን።

ፍቅር - መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ፍቅር በክርስቲያኖች ልብ ውስጥ ያፈሳል (ሮሜ 5፡5)። ይህ በዘመናት ሁሉ በግለሰብ ክርስቲያኖችና ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ለተጀመሩ አያሌ የምሕረትና የእርዳታ ተግባራት ዓይነተኛ ማብራሪያ ነው። ክርስቲያኖች ድሆችን፥ ዓይነ-ስውሮችን፥ አካለ-ስንኩላንን፥ በሽተኞችንና በዓለም ውስጥ የተለያየ ጉዳት የሚደርስባቸውን ሰዎች በመርዳት የመጀመሪያዎች መሆናቸውን ታሪክ ደግሞ ደጋግሞ ይመዘግባል። ይህም የሆነው መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ፍቅር በእነዚህ አማኞች ልብ ውስጥ ስላፈሰሰ ነው። ምእመናን ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት አኳያ ሳይሆን፥ ከራሳቸው የኃጢአት ተፈጥሮ አኳያ እንደሚኖሩ ከሚያሳዩ ግልጽ አመልካቾች አንዱ፥ ሐሜት፥ መከፋፈል፥ ውጥረት፥ ጥላቻና ይቅር አለማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖራቸው ነው።

የክርስቲያን አንድነት- መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች መካከል አንድነትንና ኅብረትን ይፈጥራል (ኤፌ. 4፡3-4)። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል የሚፈጠረው ክርስቲያኖች ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት አኳያ ሳይሆን፥ ከራሳቸው የኃጢአት ተፈጥሮ አኳያ ሲመላለሱ ነው (ሮሜ 8፡5-6)። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት፥ ይቅር መባባልና ፍቅር

ካለ በዚያች ቤተ ክርስቲያን የሚያመልኩ ክርስቲያኖች «በመንፈስ እየተመላለሱ» ናቸው ማለት ነው (ገላ. 5፡16፤ ቆላ. 3፡12-14)።

### ቀ. ለሁሉም ክርስቲያኖች በአጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ዕቅድ ምንድን ነው?

የእግዚአብሔር ሕዝቦች (ቤተ ክርስቲያን)፥ በአጠቃላይ በመጀመሪያ ሲፈጥራቸው ይኖራቸው ዘንድ ያቀደውን የኑሮና የተግባር ውበት እንዲያሳዩ ፈቃዱ ነው (ዘፍጥ. 1፡27-28ን ከኤፌ. 4፡22-24 ጋር አወዳድር)። የዚህ ዓለም ግብረ-ገባዊና ማኅበራዊ ሕይወት በኃጢአት ሙሉ ለሙሉ ተበላሽቶአል። የምንኖርበት ዓለም ግብረ-ገባዊና ማኅበራዊ ውድቀት የተጫነው ነው። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ሕዝቦች ለእርሱና ለእርስ በርሳቸው በፍቅር ላይ ተመሥርተው በማኅበረሰቡ ውስጥ በመግባባት የሚኖሩበት እጅግ የተሻለ መንገድ እንዳለ ለመግለጽ ይፈልጋል። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራስ-ወዳድና ክፉ ለሆኑ የዓለም ሕዝቦች የጽድቅና የፍቅር ምስክር ልትሆን ይገባል።

በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን «ቅዱስ ሕዝብ» ተብላለች። ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» ሲል ጽፎአል (1 ጴጥ. 2፡9)። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በከንፈራቸው የእርሱን ምስጋና ሊናገሩ [መዝ. (34)፡1]፥ እርስ በርሳቸውና ለዓለም የፍቅርንና የሰናይ ምግባርን ሕይወት ሊኖሩ ይገባል (ቲቶ 2፡14)። ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የወጠነው ታላቅ ዕቅድ ነው። በምዕራፍ ዘጠኝ ለቤተ ክርስቲያኑ ያለውን ዕቅድ በበለጠ በዝርዝር እናጠናለን።

### በ. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት ነው?

በመንፈስ ቁጥጥር ሥር መሆን ወይም በመንፈስ መያዝ በአፍሪካ የተለመደ ክስተት ነው። አብዛኛዎቹ ሰዎች በአንድ ወይም በሌላ አጋጣሚ በመንፈስ ቁጥጥር የሚኖር ሰው ተመልክተዋል። አንድ ሰው በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ሲሆን፥ ባሕርዩና ጠባዩ በሚያስደንቅ ሁኔታ ይለወጣል። እንግዳ የሆነ ሥጋዊ ጥንካሬና ጽናት ሊኖረው ይችላል። የራሱ ባልሆነ አዲስ ቋንቋ ሊናገር ይችላል። ከቅድመ-ትውልድ ወይም ከመናፍስት ትንቢቶችን ወይም መልእክቶችን ሊናገር ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ሰውየው በቢላዋ እንደ መቆረጥ ወይም በእሳት እንደ መቃጠል የመሳሰሉ አንዳንድ

ሥቃይ ሊያሳድሩ የሚችሉ ቁስሎች ላይሰሙት ይችላሉ። በመናፍስት ቁጥጥር ሥር ስለ መዋል ወደፊት በዝርዝር ይብራራል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰው በትክክል በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ፥ «በመንፈስ ተሞላ» ስለሚባልበት ሁኔታ ይናገራል። በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና በትውልድ መንፈስ ቁጥጥር መካከል አንዳንድ ነጥቦችን ማነጻጸር ይቻላል። በትውልዳዊ መናፍስት ቁጥጥር ሥር መዋል ለዚያ መንፈስ ለጊዜው ሙሉ ለሙሉ መታዘዝን ያስከትላል። እንደዚሁም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር መዋል ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለጊዜው ሙሉ ለሙሉ መታዘዝን ያስከትላል። በትውልዳዊ መናፍስት ቁጥጥር ሥር መዋል፥ ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል በአንድ በኩል በመናፍስቱ ቁጥጥር ሥር በዋለው ሰው አካባቢ የሚገኙትን ሰዎች ይነካል። በተመሳሳይ ሁኔታ በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ሥር መዋል ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል በመንፈስ ቅዱስ በተሞላው ሰው አካባቢ የሚገኙትን ሰዎች ይነካል። በትውልዳዊ መንፈስ ቁጥጥር ሥር በመዋልና በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ሥር በመዋል መካከል የሚገኙ ልዩነቶች ከሚቆጣጠረው መንፈስ ባሕርያት የሚመነጩ ናቸው።

አንድ ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ሲሞላ ባሕርዩና ጠባዩ በሚያስደንቅ ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል። ይህም ሲሆን፥ ዓሣ አጥማጁ ጴጥሮስና ዮሐንስ ክርስቶስን በገደሉት የአይሁድ መሪዎች ፊት እንዳደረጉት (የሐዋ. 4፡13) ሁሉ፥ ማናቸውም ያልተማረና ዝምተኛ ሰው እጅግ በተማሩ ሰዎች ፊት ስለ ክርስቶስ በከፍተኛ ድፍረት ሊመሰክር ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አንዳንድ ሰዎች ከፍተኛ ሥጋዊ ጥንካሬ አግኝተዋል (መሳ. 15፡14-15)። አንዳንድ ሰዎች የማያውቋቸውን ቋንቋዎች ተናግረዋል (የሐዋ. 2፡4)። አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ትንቢታዊ መልእክቶችን ተናግረዋል (ሉቃ. 1፡41-43)። ከትውልዳዊ መንፈስ በተቃራኒ፥ በክርስቲያን ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሁልጊዜም ለእግዚአብሔር ሕዝቦችና ለተሞላው ሰው በረከትን ያመጣል። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለእግዚአብሔር ክብርንና ምስጋናን ያመጣል።

በቅርቡ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የመከራከሪያ ርዕስ-ጉዳይ ሆኗል። እንደ ሌላው የእግዚአብሔር እውነት ሁሉ፥ ስለዚህም ጉዳይ እርግጠኛ ልንሆን የምንችልበት ብቸኛ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በመመርመር

ነው። ይህንንም ለማድረግ፥ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ የሚገልጹትን አያሌ ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እናጠናለን።

እንዲህ ዓይነት ብዙ ምሳሌዎች አሉ። በብሉይ ኪዳን፥ እግዚአብሔር ባስልኤልን በለየውና የመገናኛውን ድንኳን ይሠራ ዘንድ ልዩ ችሎታ በሰጠው ጊዜ፥ «የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት» ብሏል (ዘጸ. 31፡2-3)። በሙሴ ላይ ያረፈው የእግዚአብሔር መንፈስ ለሰባው የእስራኤል ሽማግሌዎች ሲታደል፥ ትንቢት ተናገረዋል (ዘኁ. 11፡25)። ጎቶንያልን (መሳ. 3፡10)፥ ጌዴዎንን (መሳ. 6፡34)፥ ዮፍታሔን (መሳ. 11፡29)፥ ሶምሶንን (መሳ. 14፡6) እና ሌሎችንም በተመለከተ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የጌታ መንፈስ በኃይል እንደ መጣባቸው ይናገራል! ይህም ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው ይታደጉ ዘንድ ነው።

በአዲስ ኪዳን፥ መልአኩ ገብርኤል ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መወለድ ለዘካርያስ ነግሮታል። ገብርኤል ዮሐንስ በእናቱ ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላ ገልጾአል (ሉቃስ 1፡15)። በመጥምቁ ዮሐንስ ልደት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ዘካርያስ ትንቢት ሲናገር በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞላ ይገልጻል (ሉቃ. 1፡67)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፥ በዕለተ-በዓለ-ሃምሳ ደቀ መዛሙርቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ስለ እግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎች ሲናገሩ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር (የሐዋ. 2፡4)። ጴጥሮስ ክርስቶስን ለሰቀሉት የአይሁድ መሪዎች ሲናገር፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደ ነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ እንረዳለን (የሐዋ. 4፡8)። እስጢፋኖስ በቁጣ ለተሞሉ የአይሁድ መሪዎች ስለ ክርስቶስ ሞት ሲናገር፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደ ነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን (የሐዋ. 7፡55)። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የዓይነ-ስውርነት ፍርድ በጠንቋዩ ኤልማስ ላይ ሲያወርድ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደ ነበር ይገልጻል (የሐዋ. 13፡9-11)።

በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ኢየሱስ፥ «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ብሏል። ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው፥ አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ እስካልተሞላ ድረስ ለወንጌል አገልግሎት ኃይል አይኖረውም።

እነዚህ ምሳሌዎች ምን ያስተምሩናል? በያንዳንዱ ምሳሌ፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለጌታ ለመሥራት ኃይልን ወይም ችሎታን ሲሰጥ

ኃይል እንደሚሰጣቸው ገልጾአል። በሉቃስ 11፡13 ኢየሱስ፥ «እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?» ብሏል። አማኞች ለሕይወታቸው እግዚአብሔር የፈቀደውን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እውነታ ቢለማመዱ መልካም ነው።

በሮሜ 8፡9 ገለጻ መሠረት፥ በትክክል የክርስቶስ የሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አለው። ይህ የሆነውም ሰውየው ደኅንነትን በሚያገኝበት ጊዜ አዲስ ልደት የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ስለ ሆነ ነው (ዮሐ. 3፡3፥ 5፤ ቲቶ 3፡5)። ይህም ሆኖ፥ ሁሉም ክርስቲያን የግድ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አይደለም። ይህማ ቢሆን ኖሮ፥ በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ ባልታዘዝን ነበር (ኤፌ. 5፡18)፤ ጳውሎስም የኤፌሶን ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ አይጸልይም ነበር (ኤፌ. 3፡15-19)።

እንደ ሌላው ጸሎት ሁሉ፥ አንድ ሰው ለመንፈስ ቅዱስ ሙላትም ከንጹሕና እውነተኛ ልብ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አለበት። ማንኛውም ግብዝነት ወይም በሰውየው ሕይወት ውስጥ የሚገኝ ኃጢአት ጸሎቱን እንዳይመለስ ያደርጋል። ኢሳይያስ 59፡1-2፥ «እነሆ፥ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፥ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም፤ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል» ይላል።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ከንጹሕና እውነተኛ ልብ ብንጸልይ፥ እግዚአብሔር ይህንን ጸሎት ለመመለስ እንደሚፈቅድ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። አሁን እንደ ተመለከትነው፥ ለክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ ማግኘት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ብንጠይቅ፥ ጸሎታችንን ሰምቶ እንደሚመልስልን ያረጋግጥልናል (1 ዮሐ. 5፡14-15)።

## በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችንን እንዴት እናውቃለን?

አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞላ እንዴት እንደሚታወቅ ክርስቲያኖች በአሳብ ይለያያሉ። አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው በሌላ ቋንቋ (የልሳን ስጦታ) እንደሚናገር ያምናሉ። ይህንንም የሚያምኑት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፥ በተለይም በዕለተ-በዓለ-ሃምሳና ከዚያም ብዙ በማይርቅ ጊዜያት፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈስ

ቅዱስ ሲሞሉ በተወሰኑ ጊዜያት በልሳን ስለ ተናገሩ ነው (የሐዋ. 2:4፤ 10:44-47፤ 19:2-6)። በአንዳንድ አጋጣሚዎች በሌላ ቋንቋ መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ምልክት ሊሆን ይችላል።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሰዎች በልሳን የተናገሩባቸውን ሁኔታዎች በጥንቃቄ ብንመረምር፥ አንድ አስፈላጊ ነገር እናገኛለን። በያንዳንዱ አጋጣሚ፥ አዲስ የሕዝብ ቡድን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይቀላቀል ነበርና፥ አዲሱ ቡድን በትክክል የክርስቶስ የአካል ክፍል እንደ ሆነ ለአይሁድ ክርስቲያኖች ለማረጋገጥ የልሳን ምልክት በተአምራዊ ሁኔታ ተሰጣቸው (የሐዋ. 11:15-17ን ከ1 ቆሮ. 1:22 ጋር አወዳድር)።

በሁሉም ሁኔታዎች የሚሠራና ዓለም-አቀፍ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መረጃ ይኖር ይሆን? በመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ የሚገልጹትን ምሳሌዎች ሁሉ ብንወስድ፥ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የሚገኘው የጋራ ባሕርይ ይህንን ይመስላል፤ በመንፈስ በተሞላው ሰው ቃላትም ሆነ ተግባራት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በግልጽ ሲሠራ ይታይ ነበር። በሌላ አባባል፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሁልጊዜም በሰውየው ቃላትና ተግባራት አማካኝነት እግዚአብሔር በመገኘቱና ኃይሉም በሥራ ላይ በመታየቱ ተለይቶ ይታወቅ ነበር። ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆኑን፥ በመንፈስ ቅዱስ በተሞላው ስብከታቸው በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመለሱት ታላቁ የዘመናችን ወንጌላዊ ዶክተር ቢሊ ግርሃም ናቸው።

የተለየ አገልግሎት የማይሰጥ ተራ ክርስቲያንስ? በዚህ ዓይነቱ ሰው ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንዳለ በምን ይታወቃል? በጥቃቅን ዕለታዊ ሕይወቱም ሳይቀር በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ሰው ክርስቶስን የሚመስል ባሕርይ (ገላ. 5:22-23)፥ ለጓደኞቹና ለቤተሰቡ ጠንካራና ውጤታማ ምስክርነት (የሐዋ. 1:8)፥ ብሎም በኃይል የተሞላ የጸሎት ሕይወት እንዳለው ሊያሳይ ይችላል (ሮሜ 8:26-27)። እነዚህ የሕይወት ብቃቶች በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ በተገለጹት እስጢፋኖስ (የሐዋ. 6:5) እና በርናባስ (የሐዋ. 11:22-24) ሕይወት ውስጥ በጉልህ ሳይታዩ አልቀሩም።

ቤተ ክርስቲያን ታድግና እየበሰለች ትሄድ ዘንድ፥ እግዚአብሔር ሕዝቦቹ ሁሉ ለሌሎች በሚሰጡት አገልግሎት ኃይል እንዲኖራቸው ይፈልጋል። ይህንንም ኃይል ለማግኘት፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያሻል። የሕዝቡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ሆነ፥

ጳውሎስ በኤፌሶን ለነበሩ ወዳጆቹ በእግዚአብሔር ሙላት ይሞሉ ዘንድ እንደ ጸለየ ሁሉ (ኤፌ. 3፡15-19)፥ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቁ ተገቢ ነው (ሉቃ. 11፡13)።

ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ ኃጢአት የማይነካው ፍጹም ሰው ይሆናል?

አንዳንድ የሕዝብ ቡድኖች አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ኃጢአት የማይነካው ፍጹም ሰው እንደሚሆን ያስተምራሉ። ሐዋሪያው ዮሐንስ፥ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» ይላል (1 ዮሐ. 1፡8)። ዮሐንስ ቀጥሎም፥ «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» ይላል (ቁ. 9)። ይቅርታ ልናገኝና ከኃጢአታችን ልንነጻ እንችላለን እንጂ፥ በዚህ ሕይወት ኃጢአት የማይነካን ፍጹማን ልንሆን አንችልም።

በመጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች በከፋ ኃጢአት መውደቃቸው አሳዛኝ እውነታ ነው። ለምሳሌ ሶምሶን የእግዚአብሔርን ፍርድ በፍልስጤማውያን ላይ ለማውረድ በመንፈስ ቅዱስ በኃይል ተሞልቶ ነበር (መሳ. 15፡14-15)፤ ይሁንና፥ ብዙም ሳይቆይ ከአንዲት ጋለሞታ ሴት ጋር ዝሙት ፈጸመ (መሳ. 16፡1)። ንጉሥ ዳዊት ከመዝሙረ ዳዊት ግማሽ ያህሉን እስኪጽፍ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ነበር (ማቴ. 22፡43-44)፤ ይሁንና፥ ዳዊት ዝሙትና የነፍስ ግድያ ፈጽሞአል! ከእግዚአብሔር በተሰጠው መገለጥ፥ ጴጥሮስ የኢየሱስን መሢሕነት በመግለጽ ታላቅ ምስክርነት ሰጠ (ማቴ. 16፡16-17)። ከዚያም፥ ጥቂት ቆይቶ ጴጥሮስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣበትን ዓላማ ለመከላከል በመሞከር የሰይጣንን ድምፅ አስተጋብቷል (ማቴ. 16፡22-23)።

የኃጢአት ተፈጥሮ ያለብን ሰብአዊ ሰዎች ስለ ሆንን (ሮሜ 7፡14-18)፥ በዚህ ሕይወት ከኃጢአት ጋር ግብግብ መፍጠራችን የሚቀጥል ሂደት ነው (1 ዮሐ. 1፡8-9)። ይሁንና፥ በዚህ ቀጣይ ትግል ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን እንድናሸንፍ የሚረዳንን መንፈስ ቅዱስ ስለ ሰጠን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን (ሮሜ 8፡12-13፤ ገላ. 5፡17-18)።

መንፈስ ቅዱስ - ክርስቲያኖችን የሚቀድሰውና የሚያበረታታው ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጡ ዘንድ የእግዚአብሔርን ልጆች ይቀድሳቸዋል - ያጠነክራቸዋል።

## በምዕራፍ 8 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ስላለው ዕቅድና መንፈስ ቅዱስ ያንን ዕቅድ ለመፈጸም እንዴት እንደሚሠራ ግለጽ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ስጥ።

2. እግዚአብሔር ለሕዝቡ በአጠቃላይ (ለቤተ ክርስቲያኑ) ያለውን ዕቅድና መንፈስ ቅዱስ ያንን ዕቅድ ለመፈጸም እንዴት እንደሚሠራ ግለጽ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ስጥ።

3. አንድ አረማዊ ተማሪ አንዳንድ የባህል እምነት ተከታዮችና ሙስሊሞች ከአንዳንድ ክርስቲያኖች የተሻለ ባሕርይ እንዳላቸው ይገልጻል። በበኩልህ እውነተኛ ክርስቲያኖች በአብዛኛው ለምን አነስተኛ የጠባይ ለውጥ ብቻ እንደሚያሳዩ እንዴት ታስረዳዋለህ?

4. አራት ተማሪዎች በሚገኙበት ቡድን ተከፋፈሉ። እያንዳንዱ ቡድን ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ የሚገልጹትን አራት ሁኔታዎች ያጥና። እያንዳንዱ ቡድን ሰውየው በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱን እንዴት እንዳወቀ የሚያመለክት መረጃ ያቅርብ።

5. ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚረዳን ተወያዩ።

6. አንዳንድ ሰዎች በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ወይም ጥንካሬና ብርታት ስላገኙባቸው ጊዜያት እንዲመሰክሩ አድርግ።

7. አንዳንድ ሰዎች በገዛ ሕይወታቸው መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊ ኃይል ወይም ተአምራት የወንጌሉን እውነታ ሲያጠናክር ስለ ተመለከቱበት ጊዜ እንዲመሰክሩ አድርግ (ዕብ. 2:3-4)

8. እግዚአብሔር ወደ አገልግሎት ስለ ጠራቸው መንገድ ይመሰክሩ ዘንድ አያሌ ተማሪዎችን ጠይቅ።

9. ቡድኑ በአገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ድሆች ክርስቲያናዊ ፍቅርና ምሕረት የሚንጸባርቁባቸውን ግልጽ አገልግሎቶች እንዲዘረዝር አድርግ። እነዚህም

ለድሆች፥ ለተራቡት፥ ለዓይነ-ስውሮች፥ ለአካለ ስንኩላን፥ ለበሽተኞችና ለመበለቶች ወይም ወላጆች ለሌሉአቸው ልጆች የሚደረጉትን አገልግሎቶች ሊጨምሩ ይችላሉ።

10. በቡድን ተከፋፍላችሁ የሐዋርያት ሥራ 8:17-24ን አጥኑ። እያንዳንዱ ቡድን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከአፍሪካ የመናፍስት፥ የምሥጢራዊ ኃይላት፥ የምትሐትና የትንበያ ጽንሰ-አሳብ ጋር እንዲያዛምድ ጠይቅ። የአስማተኛው ስምዖን ታላቅ ኃጢአት ምን ነበር? ይህስ ለአፍሪካውያን ክርስቲያኖች የሚያስተላልፈው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

11. በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በክፉ መናፍስትና በአጋንንት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

12. አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ የክርስቲያን ቡድኖች በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ጎጂ ክርክሮችን ያደርጋሉ። እነዚህ ክርክሮች ከክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ስለሚወገዱባቸው መንገዶች ተወያዩ።

## SUGGESTED FOR FURTHER READING

Graham, Billy. The Holy Spirit. London: Fount, 1980.

Green, Michael. I Believe In The Holy Spirit. London: Hodder, 1985.

Packer, J. I. Keep In Step With The Spirit. Leicester: InterVarsity Press,1984.

Packer, J. I. A Passion for Holiness. Cambridge: Crossway, 1992.

Pytches, David. Come Holy Spirit. London: Hodder, 2nd edn 1995.

Smail, T. The Giving Gift. Darton: Longman & Todd, 1994.

Stott, J. Baptism and Fullness. Leicester: InterVarsity Press, 1964.